# አንጃው በኢንጅነር ኃይሉ ሻውል ሽፋን ሥር በመንቀሳቀስ ዓላማው ገፍቶበታል

ከቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ አፈንግጠው የወጡ ጥቂት የቀድሞ የፓርቲው አመራር አባላት አዲስ ለማቋቋም ላቀዱት ፓርቲያቸው ድጋፍ ለማሰባሰብ የኢንጅነር ኃይሉ ሻውልን ስም ሽፋን አድርገው እንደሚንቀሳቀሱ የቅንጅት ፓርቲ አባላትና ደጋፊዎች ሰሞኑን ለፓርቲው ጽ/ቤት በስልክና  በግንባር እየቀረቡ በመግለጽ ላይ እንደሚገኙ ታውቋል፡፡

በዚህም መሠረት በሰሜን ወሎ ውስጥ ከሐይቅ ወረዳ ነዋሪዎች ድጋፍ እንዲያሰባስቡ በአንጃዎቹ የተላኩት አቶ አህመድ አበጋዝ የተባሉት ሰው «ከኢንጅነር ኃይሉ ጋር ታርቀናል፡፡ ጠቅላላ ጉባኤውንም የምንጠራው አብረን ነው! አሁንም ፊርማ ለማሰባሰብ የእሳቸውን ይሁንታ አግኝተናል!» በማለት ጥቂት ነዋሪዎችን በማሳመን የድጋፍ ፊርማ ያገኙ ሲሆን ፈራሚዎቹ ግለሰቡ እንዳሳሳቷቸው ሲረዱ ግን ተከታትለው ባለፈው ሳምንት ከፊሎቹ ደሴ ድረስ በመሄድ ፊርማቸውን ሲያሰርዙ ሌሎቹ ግን ሊያገኙ ዋቸው ባለመቻላቸው በፍለጋ ላይ እንደሆኑ ታውቋል፡፡

በተዛመደ መልኩ አቶ ግዛቸው ሽፈራው ዋነኛው የአንጃው አባል ወደ ሰሜን ወሎ ወልድያ ከተማ ስልክ በመደወል «መሪያችን ኢንጅነር ኃይሉ ሻውል ናቸው! ለምንድነው የድጋፍ ፊርማ የምትነፍጉን?» በማለት ሕዝቡን ለማሳመን ሰሞኑን ከፍተኛ ጥረት አድርገው እንዳልተሳካላቸው ተያይዞ ከደረሰን ዜና ለማወቅ ተችሏል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ ድጋፍ ለማሰባሰብ ወደ ሰሜን ወሎ ዞን ወልዲያ ከተማ የሄዱት አንድ የአንጃዎች ጀሌ አቶ አለባቸው አያሌው የዞኑን የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ተጠሪዎችን አግኝተው «በቀድሞ መኢአድ ተደራጅታኋል እንዴ?» በማለት ሲጠይቋቸው «እኛ መኢአድ አይደለንም! በኢንጅነር ኃይሉ ሻውል የሚመራው የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ተጠሪዎች ነን!» የሚል መልስ መጋቢት 24 ቀን 2000 ዓ.ም እንደተሰጣቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡

ሆኖም የአንጃው መልዕክተኛ ተስፋቸውን ሳይቆርጡ አሁንም በመቀጠል «ኢንጅነር ኃይሉ ሻውል ቤታቸውን በአርባ ሺህ ብር አከራይተው ወደ አሜሪካ ሄደዋል፡፡ ፈፅሞ አይመለሱም ካልሆነ ደግሞ ብርቱካን ሚደቅሳን ይዘናት እንምጣ እንዴ?» በማለት ሌላ ሃሳብ ቢያቀርቡም መንፈስ ጠንካሮቹ የቅንጅት ተጠሪዎች ሊቀበሏቸው ፈቃደኞች እንዳልሆኑ ከሥፍራው በስልክ የተላለፉ መረጃዎች አረጋግጠዋል፡፡

በምዕራብ ጎጃም ዞንም በሜጫ ወረዳ የቅንጅት የፓርላማ ተወካይ የሆኑት አቶ ባዘዘው በዜ መጋቢት 22/2000 ዓ.ም ከተማ ውስጥ እየተዘዋወሩ ሕዝቡን ሥራ ለመቀጠር የምትፈልጉ እንድትመዘገቡ ብለው  ማስፈረማቸው እንደታወቀ አንድ የቅንጅቱ ሥራ አስፈጻሚ አባል የሆኑ ፊርማው የተካሄደው ለሥራ ሳይሆን ለአዲስ

ፓርቲ ድጋፍ መሆኑን በገለፁላቸው ወቅት አብዛኛዎቹ ፈራሚዎች «በሕግ አምላክ! ስማችንን ሰርዙልን» ብለው ማሰረዛቸው ከሥፍራው ተዘግቧል፡፡ እኚህ ግለሰብ አሁንም ተስፋ ሳይቆርጡ ይህ የሥራ እድል እንዳያመልጣችሁ እያሉ ቅስቀሳቸውን ቢቀጥሉም ማስፈረሙ ያልተሳካላቸው መሆኑ ታውቋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አቶ ባዘዘው በዜ የምዕራብ ጎጃም ዞን የክልል ተመራጮችን በአካልና በስልክ እየተገናኙ ኢንጅነር ኃይሉ ወደ ኢትዮጵያ እንደማይመጡ በመደጋገም ሲናገሩ ቢቆዩም የሚያምናቸውና የሚቀበላቸው እንዳላገኙ ተጠቅሷል፡፡

በዚሁ በምዕራብ ጎጃም ዞን የፓርላማ አባል የሆኑት አቶ አዕምሮ አወቀ በደንበጫ ከተማ በተወለዱበት ቀበሌ ዘመዶቻቸውን እየተዘዋወሩ እኔ ከእናንተ የወጣሁ ልጃችሁ በመሆኔ እመኑኝ አንድ መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ሥራ ሊቀጥራችሁ ስለሚፈልግ እንድትፈርሙ እያሉ ከ25-30 የሚደርሱ ሰዎችን እንዳስፈረሙ ታውቋል፡፡

ሰሜን ጐንደርም አቶ ስዩም ማሞ የተባሉ የፓርላማ አባል ከሁለት ግለሰቦች ጋር በመሆን በየመንደሩ እየተዘዋወሩ የድጋፍ ፊርማ ለማሰባሰብ ቢሞክሩም እስከአሁን ምንም ፈራሚ ሳያገኙ ቀርተው አሁንም በዚያው ከተማ እንደሚገኙ ከሥራፍው የደረሰን ዜና ያስረዳል፡፡

አዊ ዞን ዳንግላ ከተማ አካባቢ የሄዱ የአንጃው አስፈራሚዎችን ሕዝቡ አንቀበልም እንዳላቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡

ቀደም ሲል እነ መቶ አለቃ ግርማ አማረ በጅማ ዞን የሕዝቡን ድጋፍ ለማሰባሰብ የኢንጅነር ኃይሉ ሻውልን ስም በሽፋንነት እንደተጠቀመው ሁሉ እነ ታምራት ታረቀኝና አቶ አለባቸው አያሌው በደሴ፣ ዶ/ር ኃይሉ አርአያና አቶ ሰይድ መሐመድ ፣ በኮምበልቻ ወረዳ፣ አቶ ዓለማየሁ ደምሴ በሰሜን ሸዋ ደነባ፣ መቶ አለቃ ዓለማየሁ የኔነህና አቶ ክፍሌ በአርባ ምንጭና በአካባቢው በተመሳሳይ ስልት የሕዝብ ድጋፍ ለማግኘት ሞክረው እንዳልተሳካላቸው ሰሞኑን መዘገቡ ይታወሳል፡፡